


# የሮማን ግዛት

– የጥንቷ ሮም ሁለት ዋና ዋና የታሪክ ጊዜያቶች ነበሯት። የመጀመሪያው የሮማን ሪፐብሊክ ሲሆን ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ509 አ.አ እስከ 27 አ.አ የቆየ ሲሆን በዚህ ወቅት አንድም ንጉስ አልነበረም። መንግሥት የሚመራው በተመረጡ ባለሥልጣናት ብቻ ነበር። ሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ27 አ.አ እስከ 476 አ.አ የዘለቀው የሮማን ኢምፓይር (የምእራባዊው የሮሜ ግዛት) ሲሆን መንግሥት የሚመራው በንጉሠ ነገሥት ነበር።

## የሮማን ሪፐብሊክ

– በሮማ ሪፐብሊክ ጊዜ የሮማን መንግሥት ከፍተኛ አመራሮች ቆንሱልስ [Consuls] ነበሩ። በአንድ ጊዜ ሁለት ቆንሱልስ የነበሩ ሲሆን ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላሉ። ይህ ማንም ሰው ያለአግባብ ስልጠና እንዳይዝ ያደርገዋል።

## የመጀመርያው ትርያምቭሬት [Triumvirate]

– የሮማን ሪፐብሊክስ መውደቅ የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ59 በሶስቱ የሮማውያን ጠንካራ ፖለቲከኞች ማለትም በጁሊየስ ቄሳር፣ ታላቁ ፖምፔይ እና በማርከስ ሊሲነስ ክራሰስ መካከል ጥምረት ሲፈጠር ነበር። ትርያምቭሬት ማለት የሶስትዮሽ ቅንጅት ማለት ነው። ይህ ህብረት የመጀመሪያ ትርያምቭሬት በመባል ይታወቃል። እነዚህ ሶስት ሰዎች ሮምን ገዙ። ሆኖም ክሪሰስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ53 አ.አ በጦርነት ሲሞት ፖምፔይ እና ቄሳር ጠላት ሆኑ።

## ጁሊየስ ቄሳር

– ቄሳር ሮም በሌለ ወቅት ፖምፔይ በቄሳር ላይ የፖለቲካ ድጋፍ ሰበሰበ። ወታደሮቹ ሩቢከን [Rubicon] ወንዝን አቋርጠው ወደ ሮም ሲቃረብ የእርስ በርስ ጦርነት ፈነዳ። መጨረሻ ቄሳር ፖምፔይን ድል በማድረጉ በሮም ኃያል ሰው ሆነ። የቄሳር ጠላቶች የሮማን ሪፐብሊክ እንዳይጠፋ እና ንጉሥ እንዲሆን ስላልፈለጉ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ44 አ.አ ገደሉት።

## ሁለተኛው ትርያምቭሬት [Triumvirate]

– ሁለተኛው ትርያምቭሬት ቄሳር ከሞተ በኋላ በማርክ አንቶኒ፣ ኦክታቪያን (የቄሳር ወራሽ) እና ሊፒደስ [Lepidus] መካከል ስምምነት ተፈጠረ። ሁለተኛው ትርያምቭሬት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ43 አ.አ በሮማውያን መንግሥት እውቅና አገኘ። አንዳንድ የታሪክ ምሁራን ይህ የሮማን ሪፐብሊክ መጨረሻ ነው ብለው ያስባሉ። ሁለተኛው ትርያምቭሬት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 33 አ.አ ቆይቷል። ሆኖም ኦክታቪያን ሊፒደስን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ36 አ.አ ከስልጣን በማስወገዱ መከፋፈል ተጀመረ።

## ኦክታቪያን፤ ማርክ አንቶኒን ድል ማድረግ

– ሁለተኛው ትርያምቭሬት እንዳበቃ በኦክታቪያን እና በማርክ አንቶኒን መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ። ማርክ አንቶኒ የግዛቱ በስተምስራቅ ከሰራዊቱ ጋር በነበረበት ወቅት ኦክታቪያን በሮም ውስጥ የጦር ቤዝ ሰራ። በኃላም በግብፅ ኪሊዮፓትራ አጋርነትን ያገኘውን ማርክ አንቶኒ ላይ ጥቃት መሰንዘር ጀመረ። ኦክታቪያን ማርክ አንቶኒን እና ኪሊዮፓትራ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ31 በአክትየም [Actium] ጦርነት ላይ ድል አደረገ።

## የሮማን ግዛት [Empire]

– ኦክታቪያን በሮም ጠንካራ ሰው ሆነ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ27 እራሱን አጉስተስ [Augustus] ብሎ በመሰየም የሮም የመጀመሪያው ንጉስ ሆነ። ይህ የሮም ግዛት መጀመሩን ያበሰረ ክስተት ነበር። የሮም መንግሥት በመጀመርያዎቹ ዘመን ላይ የበለፀገ ነበር። ግዛቱ ትልቅ ስፍራዎች ያዘ። ሮም በጣም ሀብታም ከተማ ሆነች።

## ከሮም ሪፐብሊክ ወደ ሮም ግዛት ሲለወጠ የነበሩ አስገራሚ መረጃዎች

– ማርክ አንቶኒ ኦክታቪያ የተባለች የኦክታቪያ እህት አገባ። ነገርግን ከኪሊዮፓትራ ጋር ግንኙነት ነበረው።

– ሁለተኛው ትርያምቭሬት የተቋቋመው ሌክስ ቲትያ [Tex Tïtïa] ተብሎ በሚጠራ ህግ ነበር። ሶስቱም አባላት ከቆንሱልስ በላይ ደረጃ ተሰጣቸው።

– ኦክታቪያ የቄሳር ወራሽ ነበር። ነገርግን የእሱ ልጅ አይደለም። የእህቱ ልጅ ነበር።

– ማርክ አንቶኒ እና ኪሊዮፓትራ ጦርነቱን እንደተሸነፉ ሲገነዘቡ ሁለቱም እራሳቸውን ገድለዋል። ሮማውያን የእርስ በርስ ጦርነት የጀመረው የቄሳር ሠራዊት ሩቢኮን [Rubïcon] ወንዝን ሲያቋርጥ ነበር። አሁን ላይ "ሩቢኮን ማቋረጥ" የሚለው አባባል የመመለሻ ነጥብ አልፈዋል እንደማለት ነው።

@nebeb_ethïopïa, ንበብ፡ ኢትዮጵያ